## ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች በሙሉ

የጠበቆች አስተዳደር እና የነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ጠበቆች የጥብቅና ፈቃድ ለማደስ በአካል ወደ ዳይሬክቶሬቱ በመምጣት እድሳት ስታደርጉ የነበረ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የእድሳት አገልግሎቱን እንደበፊቱ ወደእኛ ሳትመጡ ባላችሁበት ቦታ ሆናችሁ በኦንላየን/online/ማደስ እንድትችሉ የኢ-አገልግሎት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ወደ ስራ የገባን በመሆኑ ወደ እኛ ለመምጣት የሚወስድባችሁ ጊዜና የምታወጡት ወጪ እንዲቀር በመደረጉ እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን፡፡

በአገልግሎቱ ለመጠቀም ከታች የተጠቀሱትን ቅደም ተከተል መከተል የሚያስፈልግ ሲሆን በዚህም፡-

1.በምትጠቀሙት ኮምፒውተርም ሆነ የእጅ ስልካችሁን የኢንተርኔት ብራውዘር በመክፈት ከዛ www.eservices.gov.et ብለው ይፃፉ፣

2. Filter Services በሚለው ስር ከተዘረዘሩት አማራጮች ውስጥ Justice,Law and Grievances ሲነካ በሳጥኑ ውስጥ √ ምልክት ሲያሳይ Renewal of Licencing Advocates Participating Before Federal Court የሚለውን ሲጫኑ በሚቀጥለው Email or Phone number (e.g. +251911111111) እና Password ሲመጣ የተጠየቀው ሞልቶ Register የሚለውን መጫንና ኮድ/ቁጥር ሲመጣ ቁጥሩን መሙላትና ቀጥሎ ያለውን ፎርም መሙላት፣

3.የጥብቅና ፈቃዳቸው ይታደስላቸው የሚለውን ደብዳቤ፣የደብተር ክፍያና ሌሎች ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ፣ፈቃድ ሲወጣ የመጀመሪያው ገፅ እና አሁን ባለበት ጊዜ ፈቃዱ ከመቼ እስከ መቼ እንደታደሰ ያለበት ገፅ እና ፎቶ ግራፍ ስካን በማድረግ በዚያው መላክ፣

4. www.eservices.gov.et ሲከፈት E-Services Portal ከሚለው ፊትለፊት Services ወይም Providers የሚለውን በአማራጭ በመጠቀም ከላይ በተገለፀው መሰረት በመሙላት መላክ ይቻላል፡፡

መረጃውን በአግባቡ ሞልታችሁ ከላካችሁ ፈቃዳችሁ ታድሶ በላካችሁት አድራሻ ይላክላችኋል፡፡

**የጠበቆች አስተዳደር እና የነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**

**ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ**

ማሳሰቢያ ፡- ይህንን የአጠቃቀም መመሪያ በተቋሙ የፌስቡክ ገጽ (FDRE Attorney General የኢፌዲሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ) ወይንም በተቋሙ ድረ-ገጽ https://www.eag.gov.et በመጠቀም ማግኘት ይችላሉ